# የ2002 ዓ.ም.

# የጉራጌ ዞን እት/ግንባታ መምሪያ

# የ2002 ዓ.ም. የ1ኛ ሩብ ዓመት

# የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

ጥቅምት /2002 ዓ.ም.
ወልቂጤ ፣

## አንደኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት

## የ2002 ዓ.ም. የ1ኛ ሩብ ዓመት የክንውን ሪፖርት

1. ሪፖርት ላኪ ፡- የጉራጌ ዞን አቅ/ግ/መምሪያ
2. ሪፖርት የሚሸፍነው ጊዜ ፡- ከሐምሌ 2001 —30/01/2002
3. የታቀዱ ቁልፍ ተግባራት

- በሁሉም የመንግስት ተቋማት 4ዙር የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተተገበሩ መሠታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ / BPR / ፣
- በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘጋጀ የውጤት ተኮር ዕቅድ / BPR / እና የምዘና ውጤት የተገለፀላቸው የዞንና የወረዳ ሠራተኞች፣
- በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሠራር ፣
- በዞኑ በሁሉም ወረዳዎችና ቀበሌዎች የመልካም አስተዳደር ፖኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተጠናከረና ወደ ተግባር የተገባ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አደረጃጀት ፣
- በሁሉም የዞኑ የገጠር ቀበሌና ወረዳ መዋቅር በግንባር ቀደም አ/አደር እንዲመራ ማድረግና አሳምኖ ማሠራትን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን ለማስፋት በአማካይ ካሉ ቀበሌዎች 45 / 10% /
- ሞዴል ቀበሌ እና በተመረጡ እያንዳንዱ ቀበሌ ደግሞ በአማካይ 4 ሞዴል አ/አደሮች በቁጥር 180 እንደዚሁም ከየቀበሌው 10% ሞዴል መንደሮች ፣
- በዞን እና በወረዳ ሴክተሮች እንዲሁም በቀበሌዎች ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎች በመቀመር የተዘጋጀና የተሰራጨ አንድ የምርጥ ተሞክሮ ሰነድ ፣
- በሁሉም ቀበሌያት የሥራ አስኪያጅ የተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ የተደረገ ድጋፍ፣
- ለሁሉም ወረዳዎችና ቀበሌዎች የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት ፣
- በዞኑ ባሉ በሁሉም የፍትህ ተቋማት / ፍ/ቤት ፣ ዐቃቤ ህግ ፣ ፖሊስ ፣ ማረሚያ ቤት / የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም አተገባበር ተደራሽ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተደረገ ድጋፍና ክትትል ፣
- በኢኮቴ እቃዎች ግዥ የሚያገለግሉ ተዘጋጅተው ለ4 ጊዜ የቀረቡ ወቅታዊ ስፔስፊኬሽን እና 11 ሶፍትዌሮች ፣

- 100% በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ፣
- በሰው ሀብት ልማትና ስልጠና አቅሙ የጎለበተ የዞን የወረዳ የቀበሌና ከተማ አስተዳደር አመራርና ባለሙያ ፣
- በመልካም አስተዳደር አፈፃፀም ዙሪያ የህዝብ ፍላጎት እና ቅሬታ ለማወቅ የተደረገ የቅኝት ጥናት / Survey / ፣
- በዞኑ ባሉ ቀበሌዎች ላይ ሳይሰለጥኑ እየሠሩ ያሉ የቀበሌ ሥራ አስኪያጆችን መረጃ ተሰብስቦ ለሚመለከተው ክፍል መላክ ፣
- ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች በኢኮቴ ግንዛቤ በማግኘት ለኘሮጀክት ኘሮፖዛል ዝግጅት ፈንድ ለማፈላለጊያ የሚረዱ መረጃዎች መሰብሰብ ፣
- በኢኮቴ እቃዎች ጥገናና የማደስ ሥራ እንዲሰራ ማድረግ ፣
- በዞኑ ለሚገኙ የግል የአይሲቲ ተቋማት በ BPR ጽንሰ ሀሳብ መሠረት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፣
- በ BPR ሥልጠና ያላገኙ የዞንና የወረዳ ሠራተኞች መረጃ መሰብሰብ ፣
- የ149 የመንግስት ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በርቀት ትምህርት በድግሪና በማስተር እንዲማሩ መረጃ መላክ ፣
- በ1990 ዓ.ም. የህዝብና የቤት ቆጠራ በጉራጌ ዞን ውስጥ የሚኙ ወረዳዎች የገጠር ቀበሌ ብዛት
- 402፣ የከተማ ቀበሌ ብዛት 22 መሆኑን ተገልጿል ፣ ነገር ግን በተጨባጭ በዞናችን 410 የገጠር ቀበሌና 26 የከተማ ቀበሌዎች ያሉ መሆኑን መረጃ የሚያመለክት ስለሆነ ይህንን ክፍተት ለማስተካከል ተሞክሯል ፣

## 4. የተከናወኑ ቁልፍ ተግባራት ፣

- በሁሉም የመንግስት ተቋማት 4 ዙር የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታስቦ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት አንድ ዙር የተተገበረ መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ / BPR / 100% ፣
- በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሠራር ተዘርግቷል ፣ በመሆኑም ከሞደባ ጋር የተያያዙ የተለያዩ 4 አቤቱታዎች ቀርበው ለሁሉቱ ምላሽ ተሰቷል 100% ፣
- ለዞኑ በሁሉም ወረዳዎች ቀበሌዎች የመልካም አስተዳደር ፖኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተጠናከረና ወደ ተግባር የተገባ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አደረጃጀት ከሁለት ወረዳ ውጪ በሁሉም ተተግብሮአል 95% ፣

- በዞን እና በወረዳ ሴክተሮች እንዲሁም በቀበሌዎች ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎች በመቀመር የተዘጋጀና የተሰራጨ አንድ የምርጥ ተሞክሮ ሰነድ ፣ ለየወረዳው ተባዝቶ ተሰጥቷል 50%
- በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር ድጋፍ ተደርጓል ፣
- በሁሉም ወረዳዎችና ቀበሌዎች የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት ተዘርግቷል ፣
- በዞኑ ባሉ በሁሉም የፍትህ ተቋማት / ፍ/ቤት ፣ ዐቃቤ ህግ ፣ ፖሊስ ፣ ማረሚያ ቤት / የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም አተገባበር ተደራሽ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የድጋፍና ክትትል ሥራ ተሰርቷል ፣
- የኢኮቴ እቃዎች ግዥ የሚያገለግሉ ተዘጋጅተው ለ4 ጊዜ የቀረቡ ውቅታዊ ስፍስፊኬሽን እና 11 ሶፍትዌሮች ፣ የማጋዛት ሥራ ተሰርቷል ፣
- 100% በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግስት ሰራተኞች አጠቃላይ መረጃ ተከናውኗል ፣
- በዞን የሰው ሀብት ሥራ አመራር በሥራ ላይ የሚገኙትንና አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን ሥራ ላይ እንዲውሉ  ለማድረግ  ስልጠናና የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል
- በዞኑ ባሉ ቀበሌዎች ሳይሰለጥኑ እየሰሩ ያሉ የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች መረጃ እና እንደዚሁም በዞንና በወረዳዎች በለውጥ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክት ጥናትና ትግበራ የሥራ ሂደት ሳይሰለጥኑ የተመደቡ ሠራተኞች ስልጠና ማግኘት እንዲችሉ ለክልሉ መረጃው ተልኳል ፣
- ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች በኢኮቴ ግንዛቤ በማግኘት ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ለኘሮጀክት ኘሮፖዛል ዝግጅት ፈንድ ለማፈላለጊያ የሚረዱ መረጃዎች ተሰብስበዋል ፣
- ምላሽ ያላገኘው ለመያዶች የቀረበው ኘሮጀክት ኘሮፖዛል በማሰልጠኛ ማዕከል የአይሲቲ እቃዎች ክትትል ተደርጐ ጥያቄው በታህሳስ ወር 2002 ተጠናቅሮ እንዲቀርብ ስምምነት ላይ ተደርሷል ፣ በተጨማሪም ስለታቀዱት የፈንድ ማግኛ መንገድ ቅድመ ጥያቄዎች ለመያዶች ቀርበዋል ፣
- 11 ዲስክቶኘ ኮምፒዩተሮች ፣ 12 ላኘቶፖችና 4 ኘሪንተሮች ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል ፣
- በዞናችን ለሚገኙት የግል የአይሲቲ ተቋማት በ / BPR /  ከሚያስቀምጡው ጽንሰ ሐሳብ ጋር መራመዳቸውን በተዘጋጀ ቼክ ሊስት መሠረት ድጋፍ ተደርጓል ፣
- የ29 የዞንና የወረዳ ሴ/መ/ቤቶች መረጃ ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/አቅ/ግ/ቢሮ የአይሲቲ እቃዎች ለፍትሃዊ ስርጭት ይረዳ ዘንድ ከዞን ፋኢልና ከጤና መምሪያዎች በስተቀር 29 የወረዳና የዞን  ሴ/መ/ቤቶች መረጃውን በመሰብሰብ ለክልል ተልኳል ፣

- ለ11 ነባርና ታዳጊ ማዘጋጃ ቤቶች ሥራን የሚያቀላጥፉ 16 ሶፍትዌሮች ፍላጎትና በበጀታቸው ለማቅረብ ፍላጐታቸውን በመጠየቅ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን ፣
- በ BPR ሥልጠና ያላገኙ ሠራተኞች መረጃ ከዞን ሴክተሮችና በወዳዎች የማሰባሰብ ሥራ ተሰርቷል ፣
- የ149 የመንግስት ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በርቀት ት/ት እንዲማሩ ለውድድር ተልኮ 26 አልፈው በተጨማሪም በቀጥታ በዲግሪ 4 ፣ በማስተርስ 2 መረጃቸው ደርሶን በአግባቡ ለሠራተኞቹ ተላልፏል ፣
- በ1999 ዓ.ም. የህዝብና የቤት ቆጠራ በጉራጌ ዞን ውስጥ የሚገኙ ወረዳዎች የገጠር ቀበሌ ብዛት 402 ፣ የከተማ ቀበሌ ብዛት 22 መሆኑን ተገልፆል ፣ ነገር ግን በተጨባጭ በዞናችን 410 የገጠር ቀበሌና 26 የከተማ ቀበሌዎች ያሉ መሆኑን መረጃ የሚያመለክት ስለሆነ ይህንን ክፍተት ለማስተካከል ከሚመለከተው አካል ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እንዲስተካከል ጥረት እየተደረገ ይገኛል ፣

## 5. ያልተፈፀሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት

- በመልካም አስተዳደር አፈፃፀም ዙሪያ የህዝብ ፍላጎት እና ቅሬታ ለማወቅ የተደረገ የቅኝት ጥናት / Survey / በኘሮግራሙ መሠረት በ2ኛ ሩብ ዓመት ይጀመራል ፣
- በሁሉም የዞኑ የገጠር ቀበሌና ወረዳ መወቅር በግንባር ቀደም አ/አደር እንዲመራ ማድረግና አሳምኖ ማሰራትን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን በማስፋት በአማካይ ካሉ ቀበሌዎች በቁጥር 45 / 10% / ሞዴል ቀበሌ እና በተመረጡ እያንዳንዱ ቀበሌ ደግሞ በአማካይ 4 ሞዴል አ/አደሮች በቁጥር 180 እንደዚሁም ከየቀበሌው 10% ሞዴል መንደሮች የመምረጥ ሥራ በቀጣይ ይከናወናል ፣

## 6. የታቀዱ አብይ ዝርዝር ተግባራት ፣

- በዞኑ በወረዳዎችና በቀበሌዎች የመንግስት ተቋማት የተቀናጀ የእቅድ አዘገጃጀት ሪፖርት አቀራረብ ፣
- ግብረ-መለስ ስርዓትና የተዘጋጀ የሴክተሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት እቅድ ፣
- በሴክተሩ የተፋጠነና በተጠናከረ መንገድ የተተገበረ የስርዓት ፆታና ፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ
- በአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች ላይ ለህብረተሰቡና ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ የሴክተሩ ወቅታዊ መረጃዎች ፣
- በዞኑ በሚገኙ ኘሪፖራቶሪ ት/ቤቶች ውስጥ ለኘላዝማና ኔት ወርክ እንዲሁም የኢንተርኔት አልግሎት የተደረገ ጥገና ፣

- በየወቅቱ የተላለፉ ልዩ ልዩ መመሪያዎች ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ማድረስ ፣
- የ BPR ስልጠናዎች ዘመናዊ ከማድረግ አኳያ ለ2 ሴ/መ/ቤቶች የተደረገ ድጋፍ ፣
- በ2002 እቅድ ዝግጅትና በውጤት ተኮር እቅድ ዙሪያ ከ15 ወረዳ አቅ/ግ/ጽ/ቤቶች ለተውጣጡ ኃላፊና ምክትል ኃላፊ ጋር የተደረገ የምክክር ስብሰባ ፣
- የተቀጠሩ ባለሙያዎችን መረጃ ለክልል መላክ ፣
- ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ 3 ዓይነት ቼክ ሊስት በማዘጋጀት የዞን መምሪያዎችና ወረዳዎች ድጋፍ ማድረግ ፣
- በመምሪያው የሚገኙ የሥራ ሂደቶች የ2002 ዓ.ም. ቲም ቻርተር በማዘጋጀት ከፈፃሚዎች ጋር የመፈራረም ሥራ መሥራት ፣
- በኢኮቴ እቃዎችና በስልጠና ቁሳቁስ የተደራጀ አንድ የሥልጠና ማዕከል ፣

## 7. የተከናወኑ አብይ ዝርዝር ተግባራት ፣

- በዞኑ በወረዳዎችና በቀበሌዎች የመንግስት ተቋማት የተቀናጀ የእቅድ አዘገጃጀት ሪፖርት አቀራረብ ፣ ግብረ-መልስ ስርዓትና የተዘጋጀ የሴክተሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት እቅድ ተሰርቷል ፣
- በአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች ላይ ለህብረተሰቡና ለተጠቃሚዎች የሴክተሩ ወቅታዊ መረጃዎች በአግባቡ ተሰራጭቷል ፣
- በሁሉም የመንግስት ተቋማት ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ 3 ዓይነት ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በ7 የዞን መምሪያዎች በ6 ወረዳዎች በመሄድ የእያንዳንዱ የወረዳ ሴክተሮች በድምሩ በ17 መ/ቤቶች ድግፍና ክትትል ተደርጓል ግብረ መልሱ ተመልሷል ፣
- በወቅቱ የተላለፉ ልዩ ልዩ መመሪያዎች በሚመለከተው አካል በወቅቱ ተላልፏል ፣
- የስኩልኔት ስርጭት ለመመህራንና ተማሪዎች በስኩል ኔት ኘላዝማዎች በተደረገው አገር አቀፍ ስርጭት ሁለት ቦታዎች በአካል በመገኘት እና ሁለት ት/ቤቶች በስልክ እየተነጋገሩ ስርጭቱ እንዲሳካ ሲደግ በአንድ ወረዳ የደረሰው የጄኔሬተር ብልሽት እና የኘላዝማ ብልሽት የጥገናና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣
- የ BPR ስልጠናዎች ዘመናዊ ከማድረግ አኳያ ለ2 ሴ/መ/ቤቶች ድጋፍ ተደርጓል
- ለ 2002 እቅድ ዝግጅት በውጤት ተኮር እቅድ ዙሪያ ከ15 ወረዳ አቅ/ግ/ጽ/ቤቶች ለተውጣጡ ኃላፊና ምክትል ኃላፊ ጋር የተደረገ የምክክር ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ ተካሂዷል
- የተቀጠሩ ባለሙያዎችን መረጃ ለክልል ሙሉ መረጃቸው ተላልፏል ፣
- በመምሪያው የሚገኙ የሥራ ሂደቶች የ2002 ዓ.ም. ቲም ቻርተር በማዘጋጀት ከፈፃሚዎች ጋር የመፈራረም ሥራ ተሰርቷል ፣

## 8. ያልተከናወኑ አብይ ዝርዝር ተግባራት

ለኢኮቴ እቃዎችና ለስልጠና ቁሳቁስ የተደራጀ አንዱ የሥልጠና ማዕከል

በሴክተሩ የተፈጠሩና በተጠናከረ መንገድ የተተገበረ የስርዓተ ፆታና ፀረ-ኤች አይቪ /ኤድስ

## 9. የእቅድ አፈፃፀም በመቶኛ

በቁልፍ ውጤት 90%

በአብይት 85 %

## 10. በእቅድ አፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጐኖች

### ጠንካራ ጐን ፡-

- ድጋፍና ክትትል የተደረገላቸው ሴክተሮች በወቅቱ ግብረ መልስ መስጠት መቻሉ
- አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከየወረዳው መሰብሰብ መቻሉ ፣
- በኢኮቴ የአይቲ ልማት ለማጠናከር ከሌሎች ሴ/መ/ቤቶች በመገኘት ድጋፍና የጥገና አገልግሎት መስጠት መቻሉ ፣

## 10.2. ደካማ ጐኖች / መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች /

10.2.1. ለመምሪያዎች ድጋፍና ክትትል ከተደረገ በኃላ እንዲሻሻሉ በግብረ መልስ ተለይተው የተገለፁ ነገሮች ሙሉ በሙሉ ተሻሽለው አለመገኘታቸው ፣

10.2.2. በየተቋሙ መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ አፈፃፀሙ እንዲገመገም በተቀመጠው ኘሮግራም መሠረት ተግባራዊ ማድረግ አለመቻል ፣

10.2.3. ለወረዳዎችና ለቀበሌዎች ድጋፍ ለማድረግ የተሽከርካሪ እጥረት መኖሩ ፣

10.2.4. በመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ በተለያየ ምክንያት ያልሰለጠኑ ሠራተኞች ለማሰልጠን ምንም የተያዘ የስልጠና በጀት አለመኖሩና ክልሉም ያለመስጠቱ ፣

## 11. በእቅድ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙን ዋና ዋና ችግሮች ፣

11.1. በሙከራ የተጠኑ የሥራ ሂደቶች በሰው ኃይል ለሚፈለገው መጠንና ጥራት ያለማሟላት

11.2. ለመምሪያው የተበጀተለት በጀት ከሥራው አንፃር ከፍተኛ የሆነ የበጀት እጥረት መኖሩ

11.3. በወረዳዎችና በቀበሌዎች የሚገኙ ተቋማት በመገኘት በቂ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ አለመቻል ፣

## 12. የተወሰዱ መፍትሄዎች

12.1. በሙከራ የተጠኑ የሥራ ሂደቶች በውስጥ ሠራተኛ መድቦ በማሠራት ሙከራውን ለመተግበር ጥረት ተደርጓል ፣

12.2. የበጀት እጥረቱን ለመቅረፍ አብቃቅቶ ለመጠቀም ጥረት ተደርጓል ፣

12.3. በትራንስፖርት በመጓጓዝ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ፣

## 13. ማጠቃለያ፡-

በ1ኛ ሩብ ዓመት የነበሩ ጠንካራ ጐኖች ለማጠናከር በቀጣዩ ሩብ ዓመት የተሻለ ተነሳሽነት በመፍጠር መደበኛ የ BPR ትግበራ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል ።